# የኦሮሚያ ልዩ ተጠቃሚነትና የአመፅ አቀጣጣዩች ሴራ

**ደስታ ኃይሉ 08-03-17**

የትምክህትና የጥበት ኃይሎች ራሳቸውን ምቾት ባለው ቦታ አስቀምጠው የኦሮሚያን ልዩ ጥቅም አስመልክተው በግራና በቀኝ ተሰልፈው የሚጮኹት ለህዝቦች ጥቅም አስበው አይደለም፡፡ የጩኸታቸው መነሻና መድረሻ ህዝቦች ያገኙትን ሰላም፣ ነፃነትና እድገት በማደናቀፍ እርስ በእርስ እንዲበጣበጡ ለማድረግ ነው፡፡

የኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ጋር ያለው ልዩ ተጠቃሚነት በህገ መንግስቱ የተቀመጠ እንጂ ትምክህተኞችና ጠባቦች በየራሳቸው መንገድ እንደሚያስወሩት የትኛውንም ብሔር ለመጉዳት አሊያም ለመጥቀም አይደለም፡፡ ይልቁንም የኦሮሚያ ክልልን ህገ መንግስታዊ መብት ለማስጠበቅ የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የተለየ ምክንያት የለም፡፡ ሊኖርም አይችልም፡፡

እንደሚታወቀው ህገ መንግሥቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ ነው፡፡ በሕዝቦች መፈቃቀድና ፍላጎት እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለማጎልበት እንዲቻል በጋራ ያፈሯቸው እሴቶችና ሃብቶች እንዲሁም ትስስሮች እንዳሏቸው በማመን በታሪካቸው ሂደት ውስጥ ያጎለበቷቸውን የጋራ ጉዳዮች ይበልጥ ለማበልፀግና የተዛቡ ግንኙነቶችንም በማረም አንድ ጠንካራ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብና የጋራ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመገንባትና ለማጠናከር የታለመ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይህን በማድረግም በሀገራችን ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ፈጣንና ህዝቡ በየደረጀው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማፋጠን በራሳቸው ፈቃድና በፍላጎታቸው የመረጡት መሆኑን በፅኑ የሚያምኑበት ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን ልዩ ጥቅም በህገ መንግሥቱ እንዲሰፍር ያደረጉት የኦሮሞን ሕዝብ ጨምሮ መላው የሀገራችን ሕዝቦች መሆናቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

የአገራችን ህዝቦች የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የፌደራል መንግሥትና የክልሎች መንግስታት እንደሚኖሩ የሚደነግግ በመሆኑ የፌዴራል መንግሥቱ መቀመጫ የሆነች ከተማ መመረጥ ስለነበረበትም የኦሮሞ ሕዝብም ሆነ መላው የሀገራችን ህዝባች በኦሮሚያ ክልል እምብርት ላይ ያለችውን አዲስ አበባ ከተማን የፌዴራሉ መንግሥት መቀመጫ አድርጎ መርጧታል፡፡ ይህም በህገ መንግሥቱ እንዲሰፍር አድርገዋል፡፡

ይህንን ውሣኔያቸውን መሠረት በማድረግም በህገ-መንግቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀፅ 5 ላይ “የኦሮሚያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሐል የምትገኝ በመሆኗ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል” በማለት ደንግጓል፡፡

ይህን የአዲስ አበባን ነዋሪ ሕዝብ ጨምሮ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ የቃል ኪዳን ሠነዳቸው ያሰፈሩትን ጉዳይ በዝርዝር ሕግ መመለስ የሚያስፈልግ በመሆኑ የሕገ-መንግሥቱን መንፈስ ተከትሎ ዝርዝሩ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ ዝርዝሩን ለመሥራት ግብዓት እንዲሆን በክልሉ ገዥ ፓርቲ ኦህዴድና በኦሮሚያ ክልል፣ በአዲስ አበባ አስተዳደርና በፌዴራል

ደረጃ ከተለያዩ አካላት ጋር ውይይቶች ሲካሄዱ ቆይተው በመጨረሻ በኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ በዝርዝር ታይቶ የመንግሥት ህጋዊ ተቋማት መከረውባቸው ረቂቅ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

ይህ እውነታም ሁከት አራጋቢዎቹ እንደሚያስወሩት ሳይሆን የኦሮሚያ ክልል ልዩ ጥቅም እንዲጠበቅ የሚወጣው ህግም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን መብቶችና ጠቅሞች በምንም መልኩ የማይሸራርፍ ነው።

እንዲያውም የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ላይ ያለው ልዩ ጥቅም በመጠበቁ ምክንያት የአዲስ አበባ አስተዳደር ሕዝብና የኦሮሚያ ክልል ሕዝብ ትስስርና መስተጋብር ይበልጥ ህጋዊ መስመር ይዞ እንዲጠናከር የሚያደርግና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያጎለብት ነው፡፡

የከተማዋና የክልሉ የመንግሥት አካላትና ነዋሪ ሕዝቦችም ዘላቂ ያለው ሰላም እንዲሰፍን ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት እንዲሁም ፈጣንና ሕዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማት ተጠናክሮ እንዲቀጥልም የሚያስችል ነው፡፡

በመሆኑም ጥቂት ሃቆችን ብናነሳ እንኳን ከአገልግሎት አቅርቦት አኳያ በማህበራዊ አገልግሎቶች ልዩ ጥቅም ማለትም ከትምህርት አኳያ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የአርሦ አደሩ ልጆችን እንዲሁም አዲስ አበባ ወይም ፊንፊኔ የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ በመሆኗ ምክንያት ልጆቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማስተማር ለሚፈልጉ ዜጎች የከተማ አስተዳደሩ በአፋን ኦሮሞ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ማደራጀት እንዳለበት ረቂቅ አዋጁ አስቀምጧል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ላይ ያለው የኦሮሚያ ክልል ነዋሪ አብዛኛውን አገልግሎቱን በተለይም የሆስፒታል አገልግሎቶችን ከከተማዋ የሚያገኝ በመሆኑ በኦሮሚያ እምብርት ላይ የተቆረቆረች ይህች ከተማ ይህንን አገልግሎት ለመስጠት በእቅዷ ውስጥ ማካተት እንደሚኖርባት ተገልጿል፡፡

እንዲሁም ከማህበራዊ አገልግሎቶች የሚመደበው ሌላው የባሕል፣ የቋንቋና የሥነጥበብ አገልግሎቶች ሲሆን ከዚህ አኳያም የማህበራዊም ሆነ የኢኮኖሚ አገልግሎቶች ለማቅረብ እንዲቻል ልዩ ጥቅሙን ለማስጠበቅ በዚህ ረቂቅ አዋጅ መሠረት አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች በቋንቋቸው አገልግሎቱ እንዲቀርብ ከአማርኛ በተጓዳኝ አፋን ኦሮሞ በከተማ አስተዳደሩ የሥራ ቋንቋ ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የከተማዋ አስተዳደር የኦሮሞ ሕዝብ ባሕልና ታሪክ የሚያንፀባርቁ የባሕልና ታሪክ ማዕከላት፣ ቲያትርና ኪነጥበባትና የመዝናኛ ማእከላት የሚነገቡበትንና የሚተዋወቁበትን ሁኔታዎች የሚያመቻች ይሆናል፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ጋር በተያያዘም የከተማዋ ስያሜ ፊንፊኔ ተብሎ ስትቆረቆር በነበረው ስያሜዋ የሚጠራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዓለም አቀፍ፣ በአህጉራዊና በሀገር ደረጃ በፌዴራል መንግሥቱና በአዲስ አበባ አስተዳደር አዲስ አበባ ተብሎ የሚጠራ መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ ይህም ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው ነው፡፡

ከከተማው መሠረተ ልማት አቅርቦት፣ ከመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ጋር የተያያዘ በተፈጥሮ ሃብት ላይና በአየርና ውሃ ላይ የሚደርስ ብክለት እንዳይኖር የሚያደርግና ይህንን መብት የማስጠበቅ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሠጠው እንደሚገባ ታምኖበት በረቂቅ አዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡

እነዚህ ጥቂት የረቂቅ አዋጁ እውነታዎች የትኛውንም ወገን የማይጎዱ ይልቁንም የህገ መንግስቱን መንፈስ ተመርኩዘው የተከናወኑ ናቸው፡፡ ትምክህተኞችና ጠባቦች የትኛው ጉዳይ ሌሎችን መጉዳት ወይም መጥቀም ሊሆን እንደቻለ ለማንም የሚገባ አይደለም፡፡ እናም ይህ የትምክህተኞች ተግባር በምንም ዓይነት መንገድ ተቀባይነት የለውም።